የ ኢትዮጵያውያን ማህበር
በስዊዘርላንድ

ASSOCIATION DES
ETHIOPIENS EN SUISSE

ኢማስ .AES
Rue H. F. Amiel 20 ; 1203 Genève
emas.aes@gmail.com

# ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል !

ለውድ ኢ.ማስ አባላትና ደጋፊዎች !
ለተከበራችሁ ኢ.ትዮጵያዊያን !

ከሁሉ በፊት በቅድሚያ እንኳን ለብረሃነ ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ እያለን ለኢ.ትዮጵያ ገና መልካሙን ሁሉ እንመኛለን ። እንዲሁም በተጨማሪ ለአውሮፓውያን አዲስ አመት እንኳን በሰላም አደረሳችሁ !! ይህ አዲስ አመት የሰላም የፍቅርና የጤና እንዲሁም በስኬት የተሞላ የደስታ ዘመን እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞታችንን እንገለጻላን ፡፡ ለምንወዳት ኢ.ትዮጵያ ሀገራችን እንዲሁም ለምናፈቅረው ህዝባችን የመከራው ዘመን አክትሞ አፈናው አብቅቶ የህዝባችን ሰብእና እና እኩልነት ተከብሮ ነጻነት፣ የህግና የሀገር ልዕልና ሰፍኖ የህዝብ ውሳኔ የማይደፈርበት ገናና ኢ.ትዮጵያን የምናይበት ዘመን ያድርግልን ።

ባለፈው ሰኔ ወር ኢ.ማስን የማፍረስ ተልዕኮ ተቀብሎ በተንቀሳቀሰው ግለሰብ ላይ በፍርድ ቤት ያገኘውን ድል ለእናንተ ውድ ወገኖቻችን ማብሰራችን የሚ.ታወስ ነው ። ፍርድ ቤቱ በትክክለኛ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ ግልጽ ህጋዊና ምክንያታዊ ትንታኔዎች በማብራራት ሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ መቀልበስ እንዳማይቻል እየታወቀ ከጀርባ ሆነው በሚያዙት ወገኖች ኢ.ማስ የሚ.ያካሂ.ዱውን ፀረ ወያኔ ትግል በይግባኝ ስም ማሽመድመዱን እንዲቀጥል በተሰጠው የመጨረሻ ደቂቃ ትዕዛዝ ይግባኝ በማለት ፍርድ ቤቱን ለማደናገር ቢ.ሞክርም ነጻው የሲ.ዊስ ፍርድ ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ ከተመለከተ በኃላ ዲሴምበር 17 2010 ባስተላለፈው ውሳኔ የመጀመሪያውን መሰረታዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍትሃዊ ውሳኔ ከተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት ጋር በማጽደቅ በድጋሚ ለማህበራችን በመፍረዱ እንኳን ደስ ያላችሁ ። ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔ የአባላቱ ድምጽ እንዲከበር ከመወሰኑም በላይ ይህ ግለሰብ በኢ.ማስ ስም መንቀሳቀስ እንዲያቆም እና ሲ.ንቀሳቀስ ቢ.ገኝ በህግ እንደሚ.ቀጣ አንቀጽ ጠቅሶ ማስጠንቀቂያ አክሎ ያሳሰባል ፡፡

የግለሰቡን ስውር ተልኮ ለመረዳት ኢ.ማስ ከዚ.ህ ቀደም የመጀመሪያውን ፍርድ ውሳኔ ተመርኩዞ ያወጣውን መግለጫ ደግሞ ማንበቡ ጠቃሚ. ነው፡.፡ ኢ.ማስን በአንድ ግለሰብ ስም አስመዝግቦ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ ለሰብአዊ መብትና ለዲሞክራሲ.ያዊ ስርአት የሚ.ደረገውን ጥረት የማፈን ዋና ተልዕኮ አለመሳካቱን ሲ.ኀዘቡ ወደ ወያኔ ፕላን ሁለት ገብተው ወያኔ በዲያስፖራው ላይ ያወጀውን የመቆጣጠርና ተላጣፊ ማህበራትኝ ድርጅቶችን የመፈልፈል ዓላማ እስኪ.ሳካ ጊዜ ለመጠት; ኢ.ማስን በይግባኝ ሥም አፍኖ በመያዝ እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ ይግባኝ ቢ.ሉም ፍርድ ቤቱ ፈጣን ውሳኔ በመስጠት ኢ.ማስን ለአመታት ለማፈን ያወጡትን ፕላን አክሽፎባቸዋል ። እንዲሁም አንዳንድ የዋህ ኢ.ትዮጵያዊያንንም በፍርድ ቤት ግርግር በማደናገር ሌላ ትርምስ በመፍጠር በሃገር ወዳድ ኢ.ትዮጵያዊያን ማህል አለመተማመንን እንዲኖር ያውጡት እቅድ ዕርቃኑን ወጥቶአል ። ኢ.ትዮጵያዊያን ተጠሰበው አብይና አሳሳቢ. በሆኑ ሃገራዊ ጉዳዮቻቸው ላይ ዜጋዊና ወናዊ. አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ በመሰሪነት የተሞላ የመለያያ አጥር ለመፍጠር እስከዛሬ ያደረጉት ጥረት ማብቃቱን ላለመቀበል መተንፈሻ ጊዜ ለማግኙ ነበር የተጣረው። ፍረድ ቤቱ ይህን በመገንዘበ ይመስላል በሪጅስትር ኮሜርስ ተሯርጦ የማህበሩን ስም በድብቅ ማስመዝገብ ኢ.ማስን ለመቆጣጠር ምንም የተለየ መብት እንደማይሰጥ በመግለጽ የኢ.ማስ አባላት አመራሩን የመሾምም ሆነ የመሻር የማይገሰስ መብት እንዳላቸው በማረጋገጥ የአባላቱን ውሳኔ እንዲያከብሩና በማህበሩ ስም ማቀሳቀስ እንደማይችሉ ከማስጠንቀቂያ ጋር የወሰነው ።

ከምስረታው ጀምሮ ኢ.ማስ የተቃጣበት የማፍረስ ተልእኮ የተሸከመውን ግለሰብ ተንኮል ጠንቅቶ ስለሚ.ያውቅ በህግ ፊት አቁሙ ፈትሀን እየጠበቀ በሌላ ጉን የቆመላቸውን አብይ ተግባራት መሰሪ እቅዳቸውን ሳያግደው ተግባራዊ ሲ.ያደርግ ቆይቶአል ። ሁላችሁ እንደምታውቁት ኢ.ማስ በስዊዘርላንድ የሚ.ኖሩ ስደተኞች

ወገኖቻችን ችግር ለመፍታት ያለሰለሰ ጥረት በማድረጉ ይሄው ዛሬ የብዙ ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ ተመልሶ በሰላም መኖር ችለዋል ። በሃገራችን ኢትዮጵያም በወያኔ መንግስት በሚደረገው አፈናና ጭፍጨፋ ምክንያት በኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ ለዓለም ህብረተሰብ ለማስታወቅ ፡ የታሰሩ የተቀዋሚ ድረጅት መሪዎች ፡ ጋዜጠኞች ፡ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች እንዲፈቱ ፡ በስዊዘርላንድ ብቻ ሳይሆን በአለምአቀፍ ደረጃ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አደራጅም በመሆን ሲሳተፍ ቆይቶአል ። የ97 ምርጫ ተከትሎ በተከሰተው የወያኔ ጭፍጨፋ ለተጉዱ ወገኖቻችን ወገናዊ አጋርነቱና ተቆርቋሪነቱን ከመግለጽ ባሻገር ለሰማዕታቱ ቤተሰቦች የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ለኢትዮጵያ ክብርና ነጻነት የወደቁ ቤዛዎቻችንን በመታደግ ላይ ይገኛል ።

ከዚህ በፊት ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው ኢማስ የብሔር የዘር የጎሳ የሃይማኖት የጾታ ወዘተ ልዮነቶችን እንደውብ የሃገራችን እሴቶች ይቀበላል። ሆኖም በነዚህ ህብሮች መስተጋብር መቻቻል መፈቃቀርና መተጋገዝ የጸናውን ሃገራዊ አንድነት ለማፍረስ እነዚህን ልዩነቶች በማራገብ ወደኈ የሚያካሂደውን ሃገር አፍራሽ አካሄድ የማይቀበል፡ በዛ አንጻርም ያልተቃኘ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው ።
የኢትዮጵያውያን ማህበር በስዊዘርላንድ (ኢማስ) ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ታሪካዊ ወቅት በማገናዘብ አፍቅሮ ኢትዮጵያ ያላቸው ለሃገራችው ልዓላዊነትና አንድነት ቀናኢ የሆኑ ለህዝባችን ሰብአዊና ዲሞክራሳዊ መብት ተቆርቋርነታቸውን የሚገልጹ ኢትዮጵያዊያን ንብረት ነው ። በዚህ እምነት ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በኢማስ ዙሪያ ተሰባስበው ገንቢ ሕተዋጽኦ በማበርከት የጋራ ቤታቸውን እንዲረከቡና እንዲያዳበሩ ኢማስ በሩን ወለል አርጉ ይጠብቃቸዋል።

እንዲሁም ሌሎች የኢትዮጵያዊያን ስብሰቦች እራሳቸውን ከወያኔ ሰርጎ ገቦችና ከቅጥረኞች ነጻ ለማውጣት የኢማስ አባላት እንዳደረጉት ሁሉ በጽናትና በአስተዋይነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በስዊዘርላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ፍሬያማ የሚሆነው በአሉባልታ ሳይሆን በተግባር የተፈተኑ ጸረ ወያኔ ወገኖችን ማሰባሰብ ሲችል እና ሃገራዊ አጀንዳን አስቀድመው በጋራ መስራት ሲችሉ ብቻ ነው።

ኢማስ ሃገራችንን ከወያኔ ማነቆ ለማስጣል በተካሄደው ዕልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ በተግባር ከተፈተኑ ኢትዮጵያውያን ጋር ተባብሮ ለመስራት ዛሬም እንደወትሮው ዝግጁ ነው።

ለሃገርና ለሕዝብ ክብር እና ፍቅር ያለን የኢትየጵያ ልጆች ዕጅ ለዕጅ ተያይዘን ትግሉን እንድናጠናክር ኢማስ ጥሪውን ያቀርባል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር